# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 3 ቁጥር 4 መጋቢት ፲፬ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.

## በትግል መሞት ሕይወት

*(መጋቢትና ሚያዝያ 1969 ዓ.ም. በደርግ የቤት ለቤት አሰሳ ሰማዕታትን ምክንያት በማድረግ)*

በትግል መሞት ሕይወት
ባመጻ መሞት ሕይወት
ዳግም ትንሳኤ ልደት
የደም የድል ጎዳና
የነቹ የነሆ ፋና
የፋኖነት ምስራቹ
የታጋይነት ብስራቱ
ድል ተቀዳጅቶ መሞቱ
በሞት ሕይወት ማግኘቱ
እናንት የአብዮት ሰማዕታት
የነገ ድል ቀን ህያዋን
የነጻነት ቀይ ጮራዎች
የጭቁን ሕዝቦች ተገን
በወህኒ ሲቃ ሰቆቃ
በፋሽስቶች ጥይት ጅራፍ
በመወገር በመገረፍ
በመታደን በመጨፍጨፍ
በቆረሳችሁት ስጋ
በደማችሁት የደም ጎርፍ
የስርዓቱ እድፍ ይታጠባል
የፋሽስት ጀሌ ይደቃል
ባንዳ በደሙ ይሾቃል
ጭቁን ድሉን ይቀዳጃል።

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 3 ቁጥር 4 መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ.ም.

# በትግል መሞት ሕይወት

*(መጋቢትና ሚያዝያ 1969 ዓ.ም. በደርግ የቤት ለቤት አሰሳ ሰማዕታትን ምክንያት በማድረግ)*

በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ የካቲት አብዮት ጎላ ብሎ እንደሚታወስ ሁሉ መጋቢትና ሚያዝያ ወራትም ትልቅ ታሪክ አላቸው። የደም ታሪክ! የጭካኔ ታሪክ! የጀግና ታሪክ! የሰማዕት ታሪክ!

ኢትዮጵያ ሀገራችን አስከፊና ዘግናኝ ትውልድ ያጣችበትን የግራዚያኒ ጭፍጨፋ የካቲት 12ን በየዓመቱ ስትዘክር ወረራና የሰው ልጆች ዕልቂት ምን ያህል አስከፊ መሆኑንና ዳግም እንዳይከሰት ለማስተማር ነው። ንፁሃን በጠራራ ፀሐይ በየአደባባዩ በአካፋና በዶማ የተጨፈጨፉበት፣ በለሊት በየቤታቸው ውስጥ በእሳት የጋዩበት፣ ወራሪው የኢጣልያ ጦር ዕድሜና ፆታ ሳይለይ የተገኘ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የታረደበት ወቅት ነበር። በሀገራችን ኢትዮጵያ ዘግናኝ ጠባሳ ጥሎ ያለፈ የወረራና የቅኝ አገዛዝ ታሪክ ነው።

የሀገራችን ታሪክ በአግባቡ ባይዘገብም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በአንድ መንግሥትና ግዛት ሥር በሰሎሞናዊ አገዛዝ እርከን ውስጥ አልፋለች። ይህ አስተዳደራዊ ሰንሰለት ተበጥሶ ዘመነ መሳፍንት እስከተተካበት ድረስ በመሃሉ ብቅ ያለችው ዮዲት ጉዲት በትንሹ ለአርባ ዓመታት ኢትዮጵያን አስተዳድራለች ሳይሆን በትናለች። የታሪክ ማህደሯ እንደሚያስረዳን፡ የአክሱምን ሀውልት ጨምሮ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትንና አድባራትን አውድማለች፣ ምዕመናንና ንፁሃንን ጨፍጭፋለች። በቀጣይነት በዘመነ ዓፄ ልብነ ድንግል አገዛዝ የግራኝ መሐመድ ወረራ ተከስቶ ከፍተኛ ዕልቂት በኢትዮጵያውያን ላይ ሲያደርስ ይህም እንደ ዮዲት ጉዲት ዘመን በርካታ አብያተ ክርስቲያናትንና የኢትዮጵያን ቅርሶች አቃጥሎና አውድሞ አልፏል።

ኢትዮጵያ ከዘመነ መሳፍንት በኋላ በንጉሥ ዓፄ ቴዎድሮስ ጥረት ዳግም በአንድ ማዕከላዊ መንግሥታዊ አስተዳደር ትተዳደር ዘንድ የተጀመረው ጥረት ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ተረክበውት የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ከማስጠበቅ በተጨማሪ እርስ በርስ የነበረውን መሳፍንታዊ አገዛዝና ሽኩቻ አጥፍተውታል ቢባል ሚዛን ይደፋል። እነኚህ ንጉሣውያን አገዛዞች ታዲያ በአገዛዝ ዘመናቸው የራሳቸው ደካማ ጎን የለም ማለት አይደለም። የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘምና ለማጠናከር የሰሯቸው ጥፋቶች ቢኖርም ሀገሪቷ ከነበረችበት ኋላ ቀር የሥልጣኔ ዘመንና ተበታትኖና ተከፋፍሎ እርስ በርስ የነበረውን መሳፍንታዊ ሽኩቻ ወደ አንድ ለማምጣት የሰጡት ትኩረት ለደካማ ጎናቸው የራሱ አስተዋጽዎ አበርክቷል።

ዓፄ ምኒልክ በዘመናቸው ሥልጣኔን ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። ባቡር፣ መኪና፣ መብራት፣ የስልክ አገልግሎት፣ ትምህርት ቤት፣ ፈሳሽ የቧንቧ ውኃ፣ ወዘተ በሌላ አገላለጽ ለሀገራችን የሚያስፈልጉ መሠረታዊ የሥልጣኔ በር ከፋቾች፦ ትምህርት፣ መገናኛና የጤና ተቋሞች ጅምር እንቅስቃሴ የተጀመረው በዓፄ ምኒልክ ዘመን ነበር። ምኒልክ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት በማስጠበቅ የአንበሳውን ድርሻ ሲወስዱ ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካና የጥቁር ሕዝብ የነፃነት ኮከብ ናቸው። ትመስክር ዐድዋ !

ኢትዮጵያ ሀገራችን በሥልጣኔውም ሆነ በመሠረተ ልማት ዕድገቱ ወርቃማውን ዘመን ያጣችው በዓፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ ነበር ቢባል ሚዛን ይደፋል። ዓፄ ኃይለሥላሴ ወደ 40 ዓመት የሚጠጋ አስተዳደራቸው ከአምስቱ ዓመት የጠላት ወረራ ባሻገር ከጦርነትና የእርስ በርስ ሽኩቻ በአንፃራዊነት "የተረጋጋ" ዘመን ነበር። የመሳፍንቱ የእርስ በርስ ሽኩቻ ያከተመበት ዘመን፣ ኢትዮጵያዊነትና ብሔራዊ ስሜት በሁሉም ህብረተሰብ ዘንድ ታላቅ ግምት የተሰጠው፣ ሀገሩን በደምና አጥንቱ ጠብቆ የኖረው የአርበኞች ትውልድ ከነፃነት ማግስት ለሀገሩ ልማትና ዕድገት ፊቱን ያሳየበት፣ እጁን የዘረጋበት ወቅት ነበር። ይህንን ብርቅዬ ዘመን ንጉሡ፣ መሳፍንቱና መኳንንቱ መመልከት ተሳናቸው። እጅግ ከሚገባው በላይና ከእግዚአብሔር ባልተናነሰ መልኩ ንጉሡ መመለክን ፈለጉ፣ በፈጣሪ ስም ዕድሜ ልካቸውን ሊገዙ ከጀሉ። ለትውልድና ለሀገር የምትተርፍ ኢትዮጵያን አቅጣጫ ከማስያዝ ይልቅ የመሬት ባላባቶች ዝርፊና ድሎት በለጠባቸው።

ከተፈጥሮ ባሻገር የሥርዓቱ አቀንቃኞች መረን ያጣ ጉቦኝነትና ዝርፊያ ሕዝቡን ለችግር እያጋለጠው መጣ። ቀደም ብለው ያልጣሉት መሠረት ኃላ ላይ ቢፈልጉት፣ ጊዜ ስጡኝ ቢሉት ጊዜ ጥሏቸው ሄደ። ረሃብ የቁም ሞት ጥርሱን አግጥጦ መጣባቸው፣ በድንቁርና የተገዛው ሕዝብ ሳያስቡት ነቃባቸው፣ በጋብቻ የቆላለፉት ሥልጣናቸው ሸሻቸው። ሊጠቀሙበት ያልቻሉት ወርቃማው ዘመናቸው ከእጃቸው አመለጠ። ከእናት አባቶቹ የአርበኝነት ታሪክ፣ ከዐድዋ ኩራት፣ ከጠላት ወረራ አልገዛም ባይነት፣ ከዓፄ ዮሐንስ አንገት መቀላት፣ ከራስ አሉላ አባ ነጋ ኢትዮጵያዊነት፣ ከዓፄ ቴዎድሮስ መስዋዕትነት፣ ከዓፄ ምኒልክ ረቂቅ አመራር፣ ከነ በላይ ዘለቀ ጀግንነት ትምህርት የቀሰመው የተማረው ትውልድ ሀገርና ሕዝብን አሰልፎ ኢትዮጵያን ለልጆቿ አላቸው። በጥቂት ባላባቶች ባለ አሥርና መቶ ሺህ ሄክታር የመሬት ባለቤትነት የምትተዳደረዋ ኢትዮጵያ "መሬት ለአራሹ" ንቅናቄ ለውድቀት አበቃቸው።

የካቲት 66 መከራ፣ ግፍና ሥቃይ ላይ ያነጣጠረ እንቅስቃሴ አቅጣጫውን ስቶ ከዮዲት ጉዲት፣ ከግራኝ መሐመድ ወረራና የካቲት 12 ጭፍጨፋ በቀጣይነት የሚመደብ ፋሽስታዊ ወታደራዊ የጥፋት አገዛዝ 17 ዓመት ሀገርና ሕዝብ ገድሎና አኮላሽቶ ለተረኛ ዘረኛ የወንበዴ አገዛዝ ኢትዮጵያችንን አስረክቦ ዛሬ እደረስንበት የሀገርና ሕዝብ አጠያያቂ ህልውና ላይ ለመውደቅ በቅተናል።

በኢትዮጵያ አገዛዝ አንድ ትውልድ የጨረሰው ፋሽስታዊ ደርግ ሊታመን የማይችል እጅግ አስከፊ ያልተዘገበ ታሪክ ተሸክሟል። ደርግና ፋሽስቱ መንግሥቱ ኃይለማርያም፤ ኢትዮጵያ

በድህነቷ ኮትኩታ ያስተማረቻቸውን ልጆቿን፣ ለነገ ተስፋ ዳዴ እያሉና ቦርቀው ያልጠገቡ ታዳጊ ሕፃናቷንና ወጣት ልጆቿን እንዴት ጭጭ አደረጋቸው? እናትና አባቶች ሳይቀሩ የበላው የደርግ አገዛዝ ዕውን ኢትዮጵያን እንዴት አዳከማት? ችግኞቿን እንዴት አደረቃቸው? ገና አልተፃፈም፣ መረጃዎቹ ከሕዝብ ዓይንና ጆሮ አልደረሱም። ዕውን በደርግ በየጊዜው የሚደረግ እሥር፣ የቤት ለቤት አሠሳ፣ ነፃ እርምጃ፣ ቀይ ሽብር በተቀነባበረ መንገድና መንግሥታዊ መዋቅር ተዘርግቶለት በአዋጅ ደረጃ ሕጋዊ ሽፋን ተሰጥቶት በመላ የደርግ አባላት አመራር ሰጪነት የተካሄደ የቅርብ ጊዜ ታሪክ አይደልምን?

ጊዜ የሰጠው ደርግ አንድ ትውልድ ሲያፈራርስ ወያኔ ደግሞ አገር አያፈራረሰ ይገኛል። ሁለቱም አምባገነኖች ታሪክን ማጣመምና ጥላሸት መቀባት ባህሪያቸው ነው። ደርግ የተቀናቀኑትን፤ ሕዝባዊ ጥያቄ ይዘው ብቅ ያሉትን፤ የሲ አይ ዬ ቅጥረኛ፣ ገንጣይ፣ አስገንጣይ፣ አናርኪስት እያለ ፈጀ። በአንፃሩ ወያኔ መብት የጠየቁትን አሸባሪ፣ ነፍጠኛ እያለ እየጨረሰ ይገኛል። **<u>ለደርግና ለወያኔ ለሁለቱም ሀገራቸው ሥልጣናቸው ነው።</u>**

በሀገራችን የትግል ታሪክ ውስጥ ያበረከቱት ሕዝባዊ ተጋድሎ፣ ያሳለፉት መከራና ስቃይ፣ የከፈሉት መስዋዕትነት፣ ያልተነገረላቸውና ተመርምሮ ያልተጻፈላቸው የሕዝብ ወገኖችና የያ ትውልድ ፈርጦች በርካታ ናቸው። ታሪክን ሊያጽፍና ሊያሰባስብ ቀርቶ ሊያጠፋ ተልዕኮው አድርጎ የመጣው የወያኔ አገዛዝ ፋሽስታዊው ደርግ በ17 ዓመት አገዛዝ ዘመኑ በሀገርና በሕዝብ ላይ ያሳረፈውን ዘግናኝ የትውልድ ማጥፋት ዘመቻ በትኩሱ በቀጥታ ከጥቃቱ ሰለባዎች የሚፈለገውን ያህል እንዳይሰበሰብና እንዳይዘገብ እንቅፋት በመሆን ይኸው 25 ዓመት አስቆጠረ። ብዙ ሊናገሩና ሊጽፉ የሚችሉ የዚያ ትውልድ ቀጥተኛ ተሳታፊዎች ጊዜ እያደከማቸው፣ እድሜ እየጣላቸው ሲመጣ የግድያው ዋና ተሳታፊና ቁንጮዎች በሩ ወለል ብሎላቸው ዛሬም ያንን አሳፋሪ ሥራቸውን እንደጀብዱ ሲጽፉትና ታሪኩን ሲያወላግዱት እየተመለከትንና እየታዘብን ነው።

በሀገር አንድነት ስለማይታመሩ፣ ለሀገራቸው ክብር ሕይወታቸውን ስለሰጡ ዓፄ ዮሐንስ፣ ራስ አሉላ አባ ነጋ፣ ዓፄ ቴዎድሮስ፣ ስለ አስተዋይ አመራራቸውና ስለ ዐድዋ ገድላቸው ዓፄ ምኒልክን ትላንትም፣ ዛሬም፣ ነገም የሚነሱት እጅግ አኩሪ ታሪክ ስላላቸው ነው። ከእነሱ በርካታ ትምህርት መውሰድ ስላለብን ነው። ዛሬ የተገላቢጦሽ ሀገር ጥሎ የፈረጠጠ እራሱን ወዳድ አረመኔ ደርግ ታሪክ በአንዳንዶች ሲወደስለት መስማትና ማየት የተደረገውና የተሠራው ግፍ ይፋ አይወጣ ዘንድ መከርቸሙ ያበረከተው አስተዋጽዎ ቀላል ባይሆንም እንደ ጥንት ጀግኖቻችን፣ አርበኞቻችን ታሪክ የኛንም ትውልድ የያን ትውልድ ታሪክ ለትውልድ እናቀርባለን፣ እናስተላልፋለን።

«ያ ትውልድ ተቋም» በዚህ ዕትማችን ደርግ በመጋቢት ወር 1969 ዓ.ም. በቤት ለቤት አሰሳ የገደላቸውን በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ከፍተኛ እርከን ደረጃ ላይ የነበሩትን እንዘክራለን፣ እናስታውሳለን። መረጃዎች እንደተፈላጊነቱ አግኝተን በደርግ ዘመን በየቀኑ የተካሄዱትን ትውልድ ገዳይ እርምጃዎች ሂደታቸውንና አፈፃጸማቸውን ብንዘግብ፣ ብናስነብብ ደስ ባለን። የጊዜ ሚዛኑ ታሪክን ጥላሸት ለሚቀቡት ቢያደላም የችሎታችንን ብቅ

እናደርጋለን። ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ የእኛን ትውልድ ጀግኑትና ሀገር ወዳድነት እናስተላልፋለን። ያካሄድ ስህተት ቢኖርብንም የማናፍርበት፣ አንገት የማናቀረቅርበት በርካታ ታሪክ አለንና። አሟሟታችን እራሱ የሚያኮራ ታሪክ ነውና ደመቅ አድርገን እንጽፈዋለን። እኛ ከፋሺስት ደርግ ጋር ተባበርን ሳይሆን ታገልን ብለን ስንዘክር፣ ስንጽፍ ወረቀቱ ብዕራችንን ይቀበላል። የእኛን ሕዝባዊ መፈክሮች ብቅ ስናደርጋቸው ዘላለማዊነታቸው፣ ዛሬም አለመመለሳቸው ልክ ነበርን ያሰኘናልና እንኮራበታለን። እኛ የሰራነው ኃጢአት ስለሌለ ከድረ ገጽና ከፓልቶክ ጀርባ ሳይሆን ፊት ለፊት በመጋፈጥ ስለ ገድላችን እንተርካለን፣ እንጽፋለን፣ እንኮራለንና እነሆ የዛሬ ትውስታችን።

ልትወልድ ቀናት የቀራትን የብርሃነ ሰላም ማተሚያ ቤት ባልደረባ የስምንት ልጆች እናት ዳሮ ነጋሽ እስከ እርግዝናዋ የገደለ አገዛዝ ደርግ ነው። የሠራተኛ ማህበር መሪው ጀግናው ማርቆስ ሀጎስና የኢሕአፓ አመራር አባል ቆራጡ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ደርግ ከመጋቢት 14 ቀን እስከ መጋቢት 17 ቀን 1969 ዓ.ም. ባደረገው የቤት ለቤት አሰሳ ከተሰዉ ብርቅዬ የሴቶች፣ የላብ አደሩና የኢትዮጵያ ሕዝብ  አለኝታዎች ናቸው ሁሌም ስንዘክራቸው የደርግ አገዛዝን ገዳይነትና አረመኔነት በማስረገጥ ነው። የኢሕአፓ አመራር አባላት ዮሐንስ ብርሃኔ፣ ክፍሉ ተፈራ እና የአዲስ አበባ ኢሕአፓ ዞናል ኮሚቴ አባል ግርማቸው ለማ እና በርካታዎች በዚሁ ፋሽስታዊ የቤት ለቤት አሰሳ ከተገደሉት በርካታዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

# አዲስ ዘመን

« ኢትዮጵያ ትቅደም »


## የቀድሞ የኢ. ሠ. አ. ማ. ጊዜያዊኮሚቴሊቀመንበር በተኩስ ልውውጥ ተገደለ

(ከኢትዮጵያ ፀኖ አገልግሎት)

አዲስ አበባን ከአድጋሪያንና ከትምር ኃሳቦች በማፅዳት በተደረገው አብዮታዊ ምንጠራ ፣ በከፍተኛ ፲፩ በተበሉ ፀፋ ውስጥ ከትናንት በስቲያ ምሽት የቀድሞው የኢ. ሠ. አ. ማ. የጊዜያዊ ኮሚቴ ሊቀ መንበር የነበረው ግርቆስ ሐጐስ በእላሽ ግዶች ተገድሏል ።

ግርቆስ ሐጐስ በመኖሪያ ቤቱ ተደብቆ ብቆ እጅ አልሰጥም ከማለቱም ሌላ ለናቱኝ በተሠማሩት አባሽ ኃዶች ላይ ተኩስ በመክፈቱ በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ሊገደል መቻሉ ተገልጿል ።

ይኼውም ፀረ አብዮተኛ ቀደም ሲል በሞዝዘልድ ኩባንያና በልዩ ልዩ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ በነበረበት ጊዜ ውስ በንንዘብ ሰርቆት በየጊዜው መባረሩ ተገልጿል ።

በመድን ድርጅት ተቀጥሮ በነበረ በትም ወቅት የቀድሞው የኢ. ሠ. አ. ማ. ጊዚያዊ ኮሚቴ እንደተሰጠመ በኩ ባልኃት ገብቶ ፣ የዚሁ ኮሚቴ ጊዚያዊ ሊቀ መንበር ሆኖ ከተመረጠ በኃላ በተ ቅታ የግልገል ፋቨሰቴን የኢ. ሕ. አ. ፓ. ቡድን ቅዕዛዝ እየተከተለ በሞ ቁት ሠራተኞች መካከል ፀረ አብዮት ሚሪ ቢያዛሔድ መቆቱ ተረጋግጧል ።

በተለይም በመስከረም ወር ፲፱፻፸፯ ዓ/ም የሥራ ማቆም እድማ እንዲፈጠር በማድረግ ይኼው ፀረ አብዮት ከሠሊ ሠራተኞችን በመከፋፈልና በማወና በኢያናው ገጽ በቿው ግምድ ሥሯል

በአሰላ ጊዚ ተሰሰ ከፍቶ የተገደለው ግርቆስ ሐጐስ

## የቀድሞ የኢ. ሠ. አ. ማ...

ከሄሞው ገጽ ከሄሞው ግምድ የቦረ በድ ከፍተኛ ሽብር ማስከተሉ ታው ቋል ።

ከዚያም ወዲህ የመገበኤዎች ቡድን የሆነውን የኢ. ሕ. አ. ፓ. መሥክሮች አያገፀባረተ በግወናበድ ላይ እንሳለ ተይዞ ለጥቂት ወራት ታስር ከቆየ በኋላ ፣ በምህረት ተሰቶ ነበር ።

ነገር ግን የፀረ አብዮተኝነት ድር ጊኑን ቶግሎ በጥቁት ሕዝብ አብዮት ላይ በግመፀ የግልገል ፋቨሰቴ የኢ. ሕ. አ. ፓ. ቡድን የሚያካሒደው የነ ፍስ ግድያና የንሞ ሽብር እቀንባባሪ በመሆን ፀረ ሕዝቧ ሚራ በማኄዱድ ላይ እንዳለ ከትናንት በስቲያ ምሽት ተገድሏል ።

እንዲሁም በከፍተኛ ፲፮ በተበሉ ፀፋ ውስጥ የተሠማሩት የአላሽ ኃዶች እንድ አናርኪስት ነድለዋል ።

በሴላ በኩል በከፍተኛ ፲፩ በተበሉ ፀ፮ የተሠማሩት አላሽ ኃዶች ሙሌ ፋት አብዛኃቷ ምንጠራ ሲደሰት ወሙ ንጀዎች ፣ ሰባት ሽጉጦች ፣ ፀፋት መቶ ስላሣ ሰባት ጥይቶች ፣ ሁለት የሶር ሚፃ መነፅሮች ፣ አሥራ ሁለት የተ ይት ካርታዎች እንዲሁም አምስት የአስሌት መኪናዎችና ሁለት የፀረት ጠክ ተገኝተዋል ።

በተጨማሪም የአሰላ ኃዶኝ ፀረ ሕዝብ-ድርጊቶችን ለመፈፀም የተዘ ጋጀ ልዩ ልዩ ግኖናችን ፣ ጋዘጦችና አራት የኢ. ሕ. አ. ፓ. ግንተዎችን በዚሁ ቀበሌ ውስጥ አግኝተዋል ።

ከነዚህም መክል ግንተዎች ፣ የፕላን ንድፎችን ፣ እንዲሁም ሁለት የአስፈት መኪናዎችና አንድ ኄተ ከሁለት መቶ ሰማንያ አንድ ጥይት ጋር ሚልያን ወስደ መሰቀል በተባለ ሰው ቤት መገኘታቸው ታውቋል ።

አንዲሁም ሙሰንኝ ሚሊዮን በተ ባለች ቤት ቤት ውስጥ ደግሞ አንድ የሶር ሚፃ መነፅር ፣ ምስት ጠመንጃ ዎችና ሠፋግ ጥይቶች የተገኙ ሲሆን ፣ ምኔራፍ አብርሃ በተባለ ሰው ቤት አንድ ጠመንጃ ፣ አንድ ሽጉጥና ፵፭ ጥይቶች ተገኝተዋል ።

በከፍተኛ ፫ ተበሉ ፰ ደግሞ ከሙ ታፊት ፲፪ አከቤ ፲፭ ድረስ በተደረገው እሰሳ ፵ ጠመንጃዎችና ሽጉጦች ፣ ፶፫፲፭ ጥይቶች ፣ ፫ የሶር ሚፃ መነፅ ሮች ፣ አንድ የሶር ሚፃ ባርኔጣ ፣ ፪ ጉሪያዎች የተገኙ ሲሆን ፣ በዚሁ ቀበሌ በተንቀሳሳ ተንባር ተሠማርተ የተገኘው ቢጋል ታደሰ ቤቱ በሚፈ ተኄበት ወቅት እንብ ሰላል ጉዳት እን ዳያደርስበትና በማስት ሰማወናበድ በመሞከሩ የቀበሌው ፍርድ ቤንን ደርፃ ባር ተተኩሷል ።

በከፍተኛ ፲፫ በቀበሌ ፀን በተካሒ ደውም አብዮታዊ ምንጠራና አሰሳ ፲፫ ጠመንጃዎች ፣ ፭፭ ሽጉጦች ፣ ፭፻፲፯ ጥይቶች ፣ ፪፻ የጎሪክ ብሮች ፣ ሻምላዎች ፣ ጉሪዲዎች ፣ ቆንጨራዎ ችና ጩቤዎች ተገኝተዋል ።

***የሠራተኛው ማህበር መሪ ማርቆስ ሀጎስ*** (ምንጭ፦ አደራ ልዩ ዕትም ግንቦት 2001 ዓ.ም. የሰማዕታት ሐውልት ግንባታ ማኅበር፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ)

በከፋ ክፍለሀገር በየም አውራጃ በ1931 ዓ.ም. የተወለደው ማርቆስ ሀጐስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን አዲስ አበባ ጀኔራል ዊንጌት አዳሪ ት/ቤት ተምሯል። የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የአስተዳደር ሥራ ሥልጠና ሰጥቶና አወዳድሮ ለመቅጠር ባወጣው መመሪያ መሠረት ማርቆስ ሀጐስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀ ተወዳድሮ በአመጣው አመርቂ ውጤትና ባሳየው ችሎታ በመመረጥ ተቀጠረ።

በመቀጠል ለተወሰኑ ዓመታት ሀገር ግዛት ሚኒስቴርና አጠር ላለ ጊዜ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠርቷል። ኢምፔሪያል ኢንሹራንስ እየሠራ ባለበት ወቅት ትዳር በመያዝ ከዛሬዋ ወ/ሮ አልማዝ ገብሩ ጋር ተጋባ። በመቀጠልም ፓን አፍሪካን ኢንሹራንስ ሠርቷል። በዚህም ወቅት ነበር ወደ ሠራተኛ ማህበር የተቀላቀለው። ማርቆስ የሠራተኛውን ማህበር ከተቀላቀለ በኋላ ሙሉ ጊዜውን ለማህበሩ በመስጠት እረፍት ሳይኖረው ይተጋ ነበር።

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ትግል እራሱን የቻለ ያልተፃፈና ያልተዘገበ ታሪክ አለው። የመጀመሪያው የሠራተኞች ማህበር መሪ የአበራ ገሙ ታሪክ በቅጡ አልታየም። ከ1935 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ሠራተኞች ማኅበር ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራትና መሪዎቻቸው ለላብ አደሩ መብትና የሥራ ዋስትና ከፍተኛ ተጋድሎ አካሂደዋል።

በዘመነ ደርግ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ለመብታቸውና ለነፃ ማኅበራቸው ደህንነት እጅጉን ታግለዋል። ማኅበራቸው ነፃ ሆኖ መብታቸውን ያስከብሩ ዘንድ ከደርግ አገዛዝ ጋር ከፍተኛ ትግል ገጥመዋል። ማኅበሩ ለሠራተኛውና ለላብ አደሩ መብት በመሞገት አኩሪ የማህበር መሪዎችን አፍርቷል። ከነዚህም ዋነኛውና አንዱ የኢ.ሠ.አ.ማ. ፕሬዘዳንት የነበረው ማርቆስ ሀጐስ ነበር።

ደርግ የየካቲት አብዮትን አቅጣጫ አስቶ ሁሉንም ረግጦ ለመግዛት ከአለው ትልሙ አንፃር የሠራተኛውንም ማህበር ጨፍልቆና በራሱ ቁጥጥር ሥር አድርጎ ትግሉን ለማሸመድመድ ቢጥርም በቆራጥ መሪዎቹና ላብ አደሮች ተጋድሎ እስከ ቀይ ሽብር ዘመን ሠራተኛው ማኅበሩን ለደርግና ለመኢሶን አላስነካም ነበር። የኢትዮጵያ ሠራተኞች ከደርግ ጋር ባደረጉት የትግል ውጤት ላብ አደሩ በ1968 ዓ.ም. የሜይ ዴይ ባህሉን እጅግ በደመቀና በበላይነት ሊያከብር አስችሎታል።

በመስከረም ወር 1968 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ለተጠራውና ተግባራዊ ለሆነው የሥራ ማቆም አድማ የኢ.ሠ.አ.ማ. አስተዋጽዎ ቀላል አልነበረም። በዚህም የሥራ ማቆም አድማ ምክንያት ደርግ ዓይኑን ጥሎበት ነበርና ለ7 ወራት ማርቆስ ሀጐስን ወደ እሥር ቤት ከተተው። በእሥር

ላይ እያለም ከፍተኛ ስቃይና መከራ ደርሶበታል። ከ7ወራት በኋላም ከእሥር ሊወጣ የቻለው በዓለም ሠራተኞች ድርጅት (I L O) ግፊትና በሠራተኞች ያላሰለሰ ትግልና ጥረት ነበር።

ፋሽስታዊው ደርግ የሚታወቅበት አንድ ትውልድ መመተር ቀይ ሽብር ከመግባቱ በፊት ሥልጣን ከተቆናጠጠበት 1967 ዓ.ም. ጀምሮ ለሦስት ዓመት ቅድመ ምንጠራዎችንና ግድያዎችን ሲያካሂድ ኖሯል። **<u>ለደርግ ቀይ ሽብር ሕዝብንና ልጆቹን የማፈኑ፣ የማሠሩ፣ የማሰቃየቱ፣ የመግደሉ ከፍተኛው ደረጃ ነው።</u>** ደርግ ሥልጣን በያዘ ደቂቃዎች የሕዝቡንና የተራማጆችን መብት በአዋጅ ካገደ በኋላ የማያቋርጥ ትግል ገጥሞታል። ይህ ትግልም በተቀናጀና በተቀነባበረ መንገድ በሕዝቡ መሪ ድርጅት በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ጥላ ሥር የተካሄደ ነበር። ደርግ በተለይ ከ1967 ዓ.ም. ጥር ወር ጀምሮ ተግባራዊ የሆነውን የ"እድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ" የዘማቾች የእሥርና የግድያ ዘመቻ ሲያደርገው ወራትም አልፈጀበት። ዘማቾች በየገጠሩ ከታጠቁ ባላባት ጋር የሚያደርጉትን ግብግብና ገበሬውን የማደራጀት ሂደት ሌላ ስጋት ውስጥ ስለከተተው በመሬት ባላባቶች እያሳበበ የገደላቸው፣ በመጠለያ ቤታቸው/ካምፓቸው ያቃጠላቸው በርካታዎች ናቸው። ከዚህ ሂደት ጋር በየከተማውም ቁጥራቸው ይነስ እንጂ የሚታሠሩ፣ ደብዛቸው የሚጠፋ፣ የሚገደሉ ነበሩ። **<u>አዎ! ከ1969 ዓ.ም. ነፃ እርምጃ በፊት የደርግን ግድያ ለየት የሚያደርገው አስከሬን በየመንገዱ አለመጣሉ ብቻ ነው።</u>**

ደርግ በመጠነኛ እሥርና ግድያ ትግሉን ለማፈን ሲጥር ያ አይበገሬ ትውልድ ለሀገሩ አንድነትና ለሕዝብ መንግሥት ምሥረታ እንዲሁም ላልተገደበ ዴሞክራሲያዊ መብት ሲሟገቱና እንደውም ትግሉ እየጋለ እየጐመራ ሲሄድ የደርግ በትር በመኢሶንና ወዝ ሊግ እተወጠነው ቀጣይ ዕቅድ ተሸጋገረ። ቤት ለቤት አሰሳ።

ደርግ ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ በርካታ አሰሳዎችን አካሂዷል። ሲጀምር "የቀድሞ ዓፄ ኃይለሥላሴ ባለሥልጣናትና ባላባት የደበቁት መሣሪያ አለ" በሚል ሽፋን ሆኖ የተጀመረው የቤት ለቤት አሠሳ አድማሱንና ግዛቱን እያሰፋ ማንኛውንም ተቃዋሚ ተብሎ የሚጠረጠርን ያስስ፣ ይበረብር ገባ። በተለይ ኢሕአፓ ላይ ያነጣጠረ። ደርግ በአዋጅ መልክ ማንም ሰው ከቤቱ ሳይንቀሳቀስ ሁለት ከፍተኛ አሰሳዎች በአዲስ አበባ ከተማ አካሂዷል። በመጋቢትና ሚያዝያ ወር 1969 ዓ.ም. እነኚህ ሁለት አሰሳዎች በተቃዋሚነት የተጠረጠሩ ሰዎችን ማሠርና መግደል ዒላማው ያደረገ ሲሆን በተለይ በመጋቢቱ አሠሳ የመኢሶን ካድሬዎች በርካታ የኢሕአፓን አባላትንና በከፍተኛ እርከን ላይ የነበሩትን ያውቁ ነበርና የደርግ ሌባ ጣት/ጠቋሚ ጣት በመሆን በአሠሳው ተሠማርተው እውነትም ብርቅዬ የኢሕአፓን ዕንቁዎች ገድለዋል፣ በእጃቸው አስገብተዋል።

ከብዙ በጥቂቱ ከኢሕአፓ አመራር ዶር ተስፋዬ ደበሳይ፣ ክፍሉ ተፈራ፣ ዮሐንስ ብርሃኔ፣ መላኩ ማርቆስና ነጋ አየለ፤ በከፍተኛ እርከን ደረጃ ላይ ከነበሩት በሪሁን ማርዬ፣ ማርቆስ ሀጐስ፣ ዳሮ ነጋሽ፣ ግርማቸው ለማ. . . የመሳሰሉ የኢሕአፓ አባላት በነዚህ ሁለት አሰሳዎች ሰለባ ሁነዋል።

የደርግና መኢሶን ጥምር አመራር በ1969 ዓ.ም. ለአሰሳው በአደረጉት ዝግጅት ወደ 755 የሚደርሱ ግለሰቦች ፎቶ በየአካባቢው በመበተን በተገኙበት ይገደሉ ዘንድ ትዕዛዝ ተሰጥቷል። ከነዚህ አንዱ በቁጥር 13 የተለጠፈው ፎቶ የሠራተኛው ማህበር ፕሬዘዳንት ማርቆስ ሀጐስ ነበር።

በወቅቱ በደርግ ከሚደረጉ ክትትሎችና ማሳደድ የተነሳ በርካታዎች ማደሪያ ቤታቸውንና አካባቢያቸውን እንዲለቁ ተገደዋል። ማርቆስም በወቅቱ እንጦጦ ኪዳነ ምህረት በሚያስኬደው መንገድ ዳርቻ እሚገኘው የባለቤቱ ወላጆች ቤት ሄደል። ቤቱ ውስጥ ውሎ አላደረም ለካስ የደርግ አሳሾች ጥቆማ ደርሷቸዋል፡ ቤቱ ተከቦ የአጥሩ በር ይንኳኳል። ማርቆስ ቤቱ መከበቡን እንዳወቀ ይዟቸው የነበሩትን የተለያዩ መታወቂያዎችና ሌሎች መረጃዎች ደርግ እጅ እንዳይገቡ የውኃ እንስራ ውስጥ ይከታቸዋል። በቀጣይነትም በቤቱ ውስጥ የነበሩትን ሕፃናት በጓሮ በር እንዲወጡ ካስደረገ በኋላ ከደርግ ጅቦች ጋር ሊጋፈጥ ይዘጋጃል። ወዲያው ከከበቡት ውስጥ የመጀመሪያ ጥይት ወደ ቤቱ ሲተኮስ እሱም የምላሽ ተኩስ ይሰጣል። በመጨረሻም ሁለት ጥይት እስኪቀረው ተኩሶና ጨለማውን ተገን አድርጎ ወደ አስፋልት በመውጣት የኢሕአፓን የትግል መዝሙር በመዘመርና መፈክሮችን በማሰማት በያዘው ሽጉጥ እራሱን አጠፋ። የጀግና ሞት ሞተ። በትግል መሞት ሕይወት። የታጋይ እረፍቱ ሞቱ። ዛሬ ታሪኩ ከመቃብር በላይ ከፍ ብሏል። የማርቆስ ሞት ህያው ሆኖ ለትውልድ አስተማሪ፣ የትግል አስተማሪ፣ የሀገርና ሕዝብ ፍቅር አርኣያነቱ ይዘከር ዘንድ ጊዜ ለኢትዮጵያ የሚሆንበት ዘመን እሩቅ አይሆንም።

ማርቆስ ሀጐስና የሕግ ባለቤቱ ወ/ሮ አልማዝ ገብሩ አምስት ልጆች አሉዋቸው። ታደሰ፣ ዳዊት፣ አምሳሉ፣ ዘመነ (ሴት) እና ደጉ ይባላሉ። ማርቆስ ሀጐስ ሲሰዋ የመጨረሻው ሕፃን ደጉ የአንድ ዓመት ልጅ ነበር። ከአምስቱ ልጆቻቸው ዳዊት በሕይወት የለም ሌሎቹ በመከራ፣ በስቃይና በችግር በእናታቸው ዘንድ አድገው ዛሬ ሁሉም እራሳቸውን ችለዋል።

“የማርቆስን አደራ ተወጥቻለው” የሚሉት ባለቤቱ ወ/ሮ አልማዝ “የማርቆስ ቤተሰቦች ልጆቹን ወስደን እናሳድግ፣ አንቺ ልጅ ነሽ አግብተሽ መኖር ትቺያለሽ ብለውኝ ነበር። እኔ ግን ልጆቼንም አልሰጥ፣ ሌላ ባልም አላገባ፣ ሌላም አልወልድ ብዬ ልጆቼን አሳደግሁ። የእሱን አደራ ጠብቄ ልጆቼን በሥነ-ሥርዓት በማሳደጌና ለቁም ነገር በማብቃቴ ለሀገሬ ብድሬን መልሻለሁ። እርሱ ለሠራተኛው ሞቷል። እኔ ደግሞ ዕድለኛ ነኝ ዓላማዬ ሁሉ ተሳክቷል።” አደራ ልዩ ዕትም ግንቦት 2001 ዓ.ም.

ወ/ሮ አልማዝ ገብሩና መሰል ቤተሰባቸው እውን አስተዋሻቸው ማነው? ያ ትውልድ ስንል በሺዎች የሚቆጠሩ ቤተሰቦችን ይነካል። የደርግ ቀይ ሽብር በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ቤተሰብ አሽመድምዷል። ዛሬም ጠባሳው በበርካታ ቤተሰቦች ዘንድ አለ። ማርቆስ በሕይወት ቢኖር ዛሬ ልጆቹ የት ነበሩ? እኛ በአጋጣሚ፣ በተአምር በሕይወት ያለን የያ ትውልድ አካላት ዛሬን ትላንት ላይ ሆነን የተመለከትን ስንቶቻችን ነን? እኛ ልንኖር ማርቆስ ሀጐስ፣ ዳሮ ነጋሽ፣ ተስፋዬ ደበሳይና በርካታዎች ሕይወት ከፍለዋል። ለዛሬአችን “ድሎት” የነሱ አጥንትና ደም እንዳለበት ዕውን አስበነዋል?

አዲስ ዘመን

«ኢትዮጵያ ትቅደም»

# የተጋለጡ አናርኪስቶች በተራማጅ ኃይሎች ቁጥጥር ሥር ዋሉ

## በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት

— ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ

የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሐቀኛና ታጋይ መዝአደሮች በመሥሪያ ቤቱ አካባቢ ካለው የቀበሌ ማኅበር ታጋይ ጓዶች ጋር በመተባበር በወንጀለኛ መከላከል ተሰማሪነው ፀረ አብዮት ድርጊት ይፈጽሙ የነበሩ አሥራ አንድ የግልገል ፋሽስቱ የኢ· ሕ· ኦ· ፓ· ትየሪኞችን በትናንትናው ዕለት ኢንዲጠው በቁጥጥር ሥር እውል ዋል። ተጋልጠው በቁጥጥር ሥር ከዋሉት መካከል ምርቱ ሬቶች ናቸው። እንዲሁም ተወናብደው ለፀረ አብ ዮት ኃይል ተባባሪ የነበሩ አሥራ አምስት መዝአደር ኞችን በተግሣፅና በምክር እንዲሁም በማስጠንቀቂያ ጭምር አልፈሞቸዋል።

በትናንትናው ዕለት በማተሚያ ቤቱ ሐቀኛ ተራ ማጆችና በቀበሌ ዐ7 ታጋይ ጓዶች የተጋለጡትና በቁ በጅኛው ገጽ በጅኛው ዓምድ ይሆል

## የተጋለጡ አናርኪስቶች በተራማጅ ኃይሎች...

### በ ብ ር ሃ ን ና ሰ ላ ም ማ ተ ሚ ያ ቤ ት

ከጅኛው ገጽ ከጅኛው ዓምድ የዞረ

ማኅር ሥር የዋሉት ቀንደኛ ፀረ አብዮተኞች ባለፉት ስምንት ወሮች ውስጥ በማተሚያ ቤቱ የውይይት ክበብ ውስጥ ሐቀኛ ተራማጆች ወደ አብዮት ሠፈር ሊመል ቷቸው ያደረጉትን ጥረት ካለመቀበላቸውም ሌላ፣ በፀረ አብዮት ድርጊታቸው ቀጥለው በሐቀኛ ተራማጆች ላይ ተፅዕኖና ማስፈራራት ይፈጽሙ እንደነበር ተገልጠ አል።

በማተሚያ ቤቱ ውስጥ የተሰገሰጉት ፀረ አብዮተ ኞች በሚፈጽሙት ድርጊት የተቆጩ ብዙኃን መዝአደ ሮች የማተሚያ ቤቱ የውይይት ክበብ እንዲያጋልጣ ቸው ሲረዳም ጊዜአት ተያቄ ያቀርቡ እንደነበረም ታው ቋል።

አብዮቱ የመሣሪያን የማተሚያ ቤቱን ጭቁንመዝ አደር በሚወናበድ በየጊዜው በመውጡ ታራማጅ ጎኖጀችና በተወሰኑትም አብዮታዊ ርምጃዎች ላይ ተቃውሶ እንዲያደርግ ይገፋፉት የነበሩት እነዚሁ ቀንደኛ አናር ኪስቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ከተከላካይነት ወደ አፕቂነት በመሸጋገሩ በሐቀኛ መዝአደሮችና ታጋይ ጓዶች ተጋልጠው በቁጥጥር ሥር ውለዋል።

በፀረ አብዮት ድርጊታቸው ተጋልጠው በቁጥጥር ሥር የዋሉት የብርሃንና ሰላም ማ/ ቤት እናርኪስቶች በየጊዜው ከፈጸሙዋቸው ፀረ አብዮት ድርጊቶች መካ ከል ፣

፩/ በ1970ዓ.ም ዓ· ም· የኅብኖ መዝአደሮችን ቀን ምክንያት በማድረግ የማ/ ቤቱ መዝአደር ወልፍ በመጣ ንዝት ጊዜ የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መፈክር እን ግፅ እንዲወጣ እደርገዋል።

፪· አስከፊው የዘውድ አገዛዝ ከሥሩ ተመንግሎ የወደቀበትን መስከረም ሁለትን የፋሽስቱ የደርግባዓል ነው በማለት ህዝታዊና ልጆታቸው አዙርፈው ሲውሉ የዘው ማ/ ቤት ጭቁን መዝአደሮች ኃይል ሥላሴን እን ደሚወድ ተቆጥሮ ከጅኛው ዘመናት ጀምሮ ውስጥ ኃ የሚሰነው ብቻ ሠልፍ ወጥቷል።

፫/ በጥር ውስጥ አደጋሪ የዓረብ መንግሥታትና ፕትጣቸውን የተንጠቆት ደመላሎቹ እንነጋ ተገኝ በናት ሀገራችን ላይ በኢምፕሪያሊስቶች ርዳታ የሚያደርጉ ትን ከንቱ ሙከራ በመቃወም ጭቁን አራ ንበረ፣ መዝ አደርችና የከተማ ነዋሪዎች ሰላማዊ ወልፍ ሲያደርጉ የነበሩ ማ/ ቤት ጭቁን መዝአደሮች ግን አሁንም እኩ ርፈው ከኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ጋር ላይቆሙ በነበሩ ማ/ ቤት ውጭ ባሉ የኢ· ሕ· ኦ· ፓ· የውስጥ አርበ ኞች አናሥው ተልዕሞ ወልፍ ላይወጡ ቀርተዋል። ቢሆ ንም ሐቀኛ ተራማጆች ትንኋም ቢሆኑ የማ/ ቤቱን ዓርማ ይዘው ብሰታቸውን አሰምተዋል።(፬) በዚሁ በጥር ወር በደርግ ውስጥ ባሉ እድጎሪ የቀኝ ክንፍ የኢ· ሕ· ፓ· የውስጥ አርበኞች ተጠንስሶ በኩረው መፈን ቅለ መንግሥት የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች የመደቁውን በበዓባውን ሥርዓት አገፈልግም ብለው ተታውሞአቸ ውን ለማሰማት ሰላማዊ ሠልፍ ሲያደርጉ የዚሁ ማ/ ቤት ሠራተኞች ግን ብሰታቸውን ለማሰማት ቢፈልጉም መካከሉ ባሉ የኢ· ሕ· ፓ· ምልምል ቅጥረኞች እፍኝ ወን ተሰንመው ሳይወጡ ቀርተዋል።

፭/ እጅግ የሚያስገነው ደግሞ ከጅኛው በላይ ሠራ ተኞች በሚገኙበት መሥሪያ ቤት ውስጥ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች፣ መዝአደሮችና የከተማ ጭቁኖች አክ አንትፋ ብለው የተቆሙን የዚህን ፀረ መዝአደር ፀረ ንበሬ የሆነውን የኢ· ሕ· ኦ· ፓ·ን የተማማማ ብጣሽ ወረቀት የማ/ ቤቱ ሠራተኞች በየሳተናቸው ውስጥ ተሰግስንመግ ኙ ነው። ይህም የሚያሳየው ደግ/ ቤቱ ውስጥ ያሉት ጭቁን መዝ አደሮች መደፈራቸውን ነው ሲሉ የማተ ሚያ ቤቱ ሐቀኛ ተራማጆች በዝርዝር ገልጠዋል።

The Generation

**ነፍሰ ጡሯ ዳሮ ነጋሽ** (ምንጭ፦ ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ እውነተኛ ታሪክ፡ ቅጽ አራት፡ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡ 1991 አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ)

**በ1936 ዓ.ም. ከጉራጌ ቤተሰብ አራት ኪሎ አካባቢ የተወለደችው ዳሮ ነጋሽ ዕድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኘው የሥነጥበብ ትምህርት ቤት ተምራለች። ዳሮ በእድገቷ ንቁና ቀልጣፋ በትምህርቷም ጎበዝ ነበረች። በቀጣይነትም በንግድ ሥራ ትምህርት ቤት ተምራ በጥሩ ውጤት ተመርቃ ሥራ ለመያዝ በቅታለች።**

ዳሮ ከዘጠኝ ልጆቿ አባት አቶ ጥላሁን ተፈራ ጋር በፍቅር የተገናኙት በስነጥበብ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ሁነው ነው። ሁለቱም አንድ ክፍል ውስጥ በመሆናቸውና በወቅቱ "ቀለሜዋ" እንደሚባለው ጎበዝ ተማሪዎች ነበሩ። ይህም ለግንኙነታቸው መጐልበት ይበልጥ አስተዋጽዎ አበርክቷል። በቀለም ትምህርት ጉብዝና የተጀመረው መቀራረብ ቀስ በቀስ ወደ ልጅነት ፍቅር ተሸጋገረ። ፍቅራቸው ወደ ዘለቄታዊ የኑሮ ጓደኝነት ለማሸጋገር የትዳር ሀሳብን ያነሱት ገና ትምህርት ላይ እያሉ ነበር። በዚህም አሳባቸው በመግፋት ጥላሁን ትምህርቱን አቋርጦ ሥራ በመያዝ ዳሮ እየተማረች እሷን መንከባከብ ያዘ። በቀጣይነትም በ1950ዎቹ ሠርግ ደግሰው ተጋቡ። ዳሮም ትምህርቷን በጥሩ ውጤት ጨርሳ ሁለቱም ሠርተው ይገባሉ።

የዳሮና ጥላሁን ትዳር በፍቅር ተሞልቶ ወደ ቤተሰባዊ ሕይወት ተሸጋገረ። ልጆች ተወለዱ። ኑሮአቸውም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሞቅ አለ። የ1960ዎቹ እንቅስቃሴ ቀስ እያለ ዳሮና ጥላሁን ውስጥ ይብሰለሰል ጀመር። በተለይ በተማሪው ክፍል የዘውድ አገዛዝ ማክተም እንዳለበት የሚደረገው ንቅናቄ ከወቅቱ ኑሮ ውድነት፣ ግፍና መከራ በማጣመር የእንቅስቃሴው ደጋፊዎች ከመሆን ሊያመልጡ አልቻሉም።

መሪ ያጣው የየካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት የዘውዱን ሥርዓት ቢገረሰሰውም የተጮኸለትን ጥያቄ ሳይመልስ አምባገነንና አፋኝ ወታደራዊ አገዛዝ ሥር ሀገሪቷ ወደቀች። ሕዝባዊ ትግሉ ቀጠለ። ለተነሱ ሕዝባዊ ጥያቄዎች ተደራጅቶ መታገል የወቅቱ ጥያቄ ነበርና የሕዝቡን ጥያቄና ወቅታዊ መፈክሮችን ይዞ ኢሕአፓ ብቅ አለ። ዳሮና ጥላሁንም በፍቅራቸው፣ በትዳራቸው፣ በቤታቸው ውስጥ ኢሕአፓን አስገቡ። ቤት ለኢሕአፓ አሉ።

ዳሮ ከንግድ ሥራ ት/ቤት ከተመረቀች በኋላ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲና በሂልተን ሆቴል ፕሮጀክት ውስጥ ሰርታለች። በ1965 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኛ ሆናለች። በዚህ መሥሪያ ቤት ውስጥ ሆና ጠንካራ የትግል ስሜት በማሳየት የእንቅስቃሴው ተሳታፊ ሆናለች።

ዳሮ ነጋሽ እንደ ኢሕአፓ አባልነቷ በህቡዕ ብትንቀሳቀስም የህጋዊ መድረኮችም ንቁ ተሳታፊ ነበረች። የቀበሌ ሂሳብ ሹም፣ የሠራተኛ ማህበራት ኢንዱስትሪ ተወካይ፣ የሚይ ዴይ በዓል አከባበር ዝግጅት ኮሚቴ አባል፣ የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ሆና ሰርታለች። በደርግ መስከረም 2 በዓል ዝግጅት ሳይቀር ተሳታፊ ሆናለች። በመጀመሪያው የደርግ ዓመት በዓል ግብዣ ላይ ሠራተኛውን ወክላ በቤተ መንግሥት ተገኝታ ነበር። ይህም አጋጣሚ የደርግ አባላቱን ቀርቦ ለማየት ዕድል ሰጥቷታል።

ዳሮ ለሠራተኛው ደሞዝ ጭማሪ በመጠየቋና ለመሠረታዊ መብቶቻቸው በመታገሏ ለእሥር ተዳርጋለች። ጊዜውም ደርግ ለማስፈራራት አንዳንዶችን እያሠረ የሚለቅበት ወቅት ስለነበር በሠራተኛውና በተቆርቋሪዎች ጉትጐታ ወዲያው ተፈትታለች። ሠራተኛውም በክብር ተቀበላት።

ዳሮ ሠራተኛው ከየትኛውም አቅጣጫ ለሚደርስበት ጥቃት ግንባር ቀደም ተፋላሚ ሆነች። የደርግ ለውጥ ሀዋርያ በተለያዩ መድረክ መሠረታዊ የሠራተኛውን ጥያቄዎች አድበስብሰው ሲያልፉ ዳሮ ዋናዋ ተከራካሪና ተጋፋጭ በመሆኗ ጥርሳቸውን እየነከሱ የመጡባት የደርግ አካላት ቀላል አልነበሩም።

ዳሮ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ፣ ታከተኝ ሳትል ለሠራተኛው መብት ሞግታለች። የቤተሰብ ኃላፊነቷና የልጆች እናት መሆኗ እንኳ ከዓላማዋና ከትግሏ ፈቀቅ ያላደረጋት ብርቅዬ የሴቶች እህቶቻችን ጀግና ነበረች።

ደርግ በህጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የብዙኃን ድርጅቶችን ማለትም የወጣቶች ማህበር፣ የሴቶች ኮሚቴን፣ የመምህራን ማህበርን፣ የሠራተኛው ማህበርን ማዋከብና መዝጋት በከፍተኛ ሁኔታ ተያያዘው። ይህ የደርግ ጫና አንዳንድ የሙያ ማህበራት በህቡዕ እንዲደራጁ አስገድዷቸዋል። በዚሁም መሠረት የሠራተኛው ማህበር ኢሠአማ የደርግ በትር ስለተወረወረበት በህቡዕ መንቀሳቀስ በማስፈለጉ የኢትዮጵያ ላብ አደሮች አብዮታዊ ማህበር (ኢላአማ) በምስጢር እንዲቋቋም አስገድዷል። ይህ የኢሕአፓ አካል ድርጅት የሆነው ኢላአማ ምሥረታ የመጀመሪያው ስብሰባ የተካሄደው በዳሮ ነጋሽ ቤት ነበር።

ዳሮ በ1968 ዓ.ም. ሜይ ዴይ በጣም ትታወሳለች። ደርግ የሠራተኛውን እንቅስቃሴ ስለሚፈራ በዓሉን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ለማክበር ይፈልጋሉ። የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኞችን ለመቀስቀስ በቅርቡ አብዮቱና ትዝታዬ (አብዮቱና ድንቁርናዬ ይመጥነዋል) በሚል ዳግም ያ ትውልድ ላይ በተለይ ኢሕአፓ ላይ ያላቸውን ንቀትና ቁጭት በሹፈትና ፌዝ ያስነበቡት ፍስሃ ደስታ ነብሩ የመጡት። በስብሰባው በሜይ ዴይ በዓል አከባበር ሠራተኛው ይዞ መውጣት ያለበትን መፈክር በማሳሰብ በመንግሥት በኩል የተዘጋጁትንና በየመሥሪያ ቤቱ የተበተኑትን ይዞ መውጣት እንዳለባቸው ሲደሰኩሩ ቆፍጣናዋ ዳሮ ነበረች የተጋፈጠቻቸው።

"...ልናገር የምፈልገው ነገር ሜይ ዴይ የሠራተኛው በዓል መሆኑን ብቻ ነው። ስለዚህ በበዓሉ ላይ ምን ማድረግ እንዳለበትና ምን ዓይነት መፈክር እንደሚያዝ ሊነገረው አይገባውም። ሠራተኛው እራሱ ያውቀዋል..." በማስቀጠልም

"...ሁሉንም ለእኛ ተዉልን። በዓላችንን በደንብ እናከብረዋለን። መፈክራችንንም እኛው እናዘጋጃለን።" በማለት ነበር ዛሬ በእርጉዝ ደም ለሚያሾፉት ፍስሃ ደስታና ተከታዮቹ ምላሽ የሰጠችው።

ዳሮ በ1968ቱ የሜይ ዴይ በዓል ውስጥ ደምቃ ታየች። "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት!" የሚለውን መፈክር ከፊት አስይዛ እሷ በራሪ ወረቀቶችን እየበተነች ሰልፉን በግምባር ቀደምትነት በመምራት በሺህ ከሚቆጠሩ ሠራተኛ ወገኖቿ ጋር ድምፃቸውን ያሰማሉ። ለላብ አደሩ ይጮኻሉ።

ዳሮ ነጋሽ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ውስጥ የትግሉ ግምባር ቀደም ተዋናይ ሆነች። አብዛኛው የማተሚያ ቤቱ ሠራተኞች ለመብታቸው ተሟጋች ሆኑ። በህቡዕ ድርጅታቸው ኢላአማ ሥር ተሰባሰቡ። ለዚህ ደግሞ የዳሮ ድርሻ የላቀ ነበር።

ፋሽስታዊው ደርግ በወጣቱ፣ በሴቶች፣ በተማሪው፣ በላብ አደሩ፣ በቢሮ ሠራተኛው፣ በታዳጊ ሕፃናት፣ በእናቶች፣ በአባቶች በአጠቃላይ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ የተጠላ የመከራ አገዛዝ ነበር። በዓለምና በአፍሪካ በወቅቱ ብቅ እንዳሉት ወታደራዊ አምባገነንና ገዳይ መሪዎች ደርግ ኢትይጵያ ላይ የተከመረ የቁጣና የመከራ ዘመን ነበር። ደርግ ሕዝባዊ ድጋፍን በመሳሪያ ማግኘት እንደማይችል ቢገነዘበውም መረን በለቀቀ ጭፍጨፋ አንገት ማስደፋት ግና እንደማያቅተው ተገንዝቧል። ለዚህም ሥልጣን ጥማቱ ከሕፃን እስከ አዛውንት፣ ነፍሰ ጡር እናቶችን ሳይቀር በጅምላ የገደለው። ይህንን አይበገሬ እንቅስቃሴ በአለው የመሳሪያ አቅሙ ተጠቅሞ የተሸማቀቀና የቁም ሞት የሞተ ኅብረተሰብ ገዛው፣ አስተዳደርን ብሎ ፉከራ ድንቁርና ካልሆነ ሌላ ምን ይሰኛል? እና ለደርግ አብዮት ፦ ግድያ፣ ሴሰኝነት፣ ድንቁርናን ያጣመረ ጉዞ ነበር ቢባል ይመጥናቸዋል።

በደርግ የገዳይነት ሂደት ሁለተኛ ደረጃ ቤት ለቤት እያሰሱ መድፋት የሚለው "ዘመቻ መንጥር"፣ "ዘመቻ ደምስስ" ከፍተኛው ደረጃ መጋቢትና ሚያዝያ 1969 ዓ.ም. ሲካሄድ በርካታ ወገኖችን በቀናት ውስጥ ሲቀጥፍ ኢሕአፓ ብርቅዬ አመራሩን ያጣበት ነበር። እንደ ግርማ ከበደ ዓይነት ገዳዮች ደርግና መኢሶን የወለዱበት፣ ኮትኩተው ያሳደጉበት ዘመን ነበር። ልትወልድ ሳምንታት የቀራት ብርቅዬዋ ታጋይ ዘጠነኛ ልጇን በዘጠኝ ወሩ ይዛው ትሄድ ዘንድ በደርግ የተረሸነችበት ቀን መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም.።

እውን ኢትዮጵያ ለልጆቿ አልቅሳለች? በአረመኔው የደርግና የመኢሶን ዱላ ግርማ ከበደ በአደባባይ የተገደለችው ነፍሰ ጡር ዳሮ ነጋሽ ባለቤት አቶ ጥላሁንና ጥላቸው የሄደችው ስምንት ልጆቿ ታሪክ ተቀብሮ ይቀር ዘንድ ይገባልን? ዳሮ ነጋሽ "በትግል መሞት ሕይወት" ያልነው ትላንትም፣ ዛሬም ወደፊትም ትውልድ ገና ያነሳሻል፣ የሴቶች ሐውልት ነሽ፣ የጭካኔ ጥልቀቱን ማሳያ ነሽ፣ ፋሽስታዊ ዘመን ዳግም እንዳይደገም ዳሮ ነጋሽ ትምህርት ቤት ነሽ።

መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም. ከጠዋቱ አራት ሰዓት አካባቢ የአራት ኪሎና አካባቢው ከፍተኛ 14ቱ አረመኔው ግርማ ከበደ ከአጃቢዎቹ ጋር ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሰተት ብሎ ገብቶ ሠራተኞቹን ለስብሰባ እንደሚፈልግ ተናገረ። ...ከተሰበሰበው ሰራተኛ መሀል የስም ዝርዝሩን እያነበበ አስወጣ። ዘጠኝ ብቻ ተገኙ።

ዳሮ ነጋሽ ከዘጠኙ መሀል አንዱ ብትሆንም ስብሰባው ላይ አልነበረችም። እስር ቤት ለሚገኘው ባሏ ስንቅ አቀብላ አርፍዳ ስትመጣ የውጭ በር ላይ ጠብቀው ነበር የያዟት።...

እንዲሁም በመጋቢት 15 ቀን 1969 ዓ.ም. አዲስ ዘመን ጋዜጣ "...በማተሚያ ቤቱ ሐቀኛ ተራማጆችና በቀበሌ 07 ታጋይ ጓዶች የተጋለጡት ቀንደኛ ፀረ አብዮተኞች በቁጥጥር ሥር ውለዋል።" የሚለውን ዜና ይዞ ወጣ።

ጋዜጣው ይህንን ዜና ይዞ በወጣበት ዕለት ዘጠኙ ሠራተኞች ቀድመው ተረሽነው፤ ሬሳቸው ሜዳ ላይ ተዘርግቶ፤ ህዝቡን ዕንባ እያራጨ ነበር።...ከዳሮ ጋር ሴቶች ሦስት ሲሆኑ ወንዶች ስድስት ናቸው። የአንድ ሴት ጡትና የአንድ ወንድ ብልት ተቆርጦ ወድቋል። መልካቸው እንዳይታወቅ ዓይናቸው ጠፍቷል፣ ፊታቸው ተጨፍጭፏል።...

የዳሮ ነጋሽ ሬሳ በህዝቡ ግፊት ወደ ሀኪም ቤት ተወሰደ። ሽል እንደያዘች አትቀበርም። ወደዚህ ዓለም ለመምጣት ጥቂት ቀናት የቀሩት ህፃን በሕይወት መኖር ያለመኖሩ መታወቅ አለበት። ምናልባት ለጉድ ቢተርፍስ?. . . ሕፃኑ ትንፋሹን ይዞ ከማህፀኗ ውስጥ ብቅ አለ። የእንግድነት ድምፁንም አሰማ። ይሁን እንጂ ብዙ አልቆየም። በመከራ ይዞአት የመጣው የሲቃ ነፍስ ወዲያው ጭልጭል ብላ ጠፋች።

ከነፍሰ ጡሯ ዳሮ ነጋሽ ጋር በፋሽስቱ ደርግና መኢሶን ቀኝ እጅ አረመኔው ግርማ ከበደ የተረሸኑት የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኞች አቶ ጥላሁን ገ/ማርያም፣ አቶ ብርሃኑ በላቸው፣ አቶ ፀሐይ ኃይለ ሥላሴ፣ አቶ ኃይሉ አበበ፣ ወ/ት ወርቅነሽ ካብትህይመር፣ አቶ ዮሐንስ አውግቸው፣ ወ/ት ዘውድነሽ ዋና እና አቶ ጥላሁን በቀለ ነበሩ።

ዳሮ ነጋሽ በተገደለች በአሥራ አምስተኛው ቀን ደርግ በሕዝብ ግፊት ባለቤቷን አቶ ጥላሁንን ከእሥር ለቀቀው። በመሪር ሐዘንና በዕድሜ ልክ ፀፀት ስምንት ልጆቻቸውን እየዬ እያለ አሳድጓል። ይህ ነው እንግዲህ የሚመፃደቁበት የደርግ አብዮት። ትውልድ የመተረ አብዮት። ደርግ አርማው ግድያ። በ60ዎቹ የዓፄ ኃይለሥላሴ ባለሥልጣናት የጀመረው ግድያ ሕዝብና ልጆቹ ላይ ሲጨፍር ኖሮ በመጨረሻ ሰዓቱ የራሱን ጄኔራሉች መደምደሚያ አድርጎ የተገረሰሰ "የሞት ታላቅ ወንድም" ቢባል ለደርግ ይመጥነዋል።

የነ ዳሮ ነጋሽ ግድያ በወቅቱ በተለይ በአራት ኪሎና አካባቢው ነዋሪ እንዲሁም በብርሃንና ሰላም ሠራተኞች ዘንድ የፈጠረውን መሪር ቁጣና እንቅስቃሴ ደርግ ለማለዘብ ሲል ሳይወድ በግድ ግርማ ከበደንና ግብረአበር ገዳዮችን አረመኔ በማለት ሊረሽን ተገዷል። አረመኔው ግርማ ከበደ የደርግንና መኢሶንን ጣምራ ትውልድ የማጥፋት እርምጃ ቀደም ብሎ በመጀመሩ ተጮኸበት እንጂ በቀጣይነት ደርግና መኢሶን በርካታ ምትክ ግርማ ከበደዎችን በየቀበሌው፣ ከፍተኛው፣ በየወረዳው፣ አውራጃና ክፍለሀገራት አፍርተው አጥቂነታቸውን በጭፍጨፋ ገፍተውበት እጃቸውን በሕዝብ ልጅ ደም ታጥበዋል።

« . . . የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ዩላጌትና ትግል፣ በአ ብዙታችን ጉዳና ገፍተው ብሔ ራዊ ነፃነታቸ የተከበረ፣ እዲሊታ ሕዝባዊትና ዲሞክራሲያ ኢትዮ ጵያ እንድትገነባ ነው. . . »

# አዲስ ዘመን

አዲስ ባንክ ADDIS BANK

« ኢትዮጵያ ትቅደም »

## በአረመኔው ግርማ ከበደና በግብረ አበሮቹ ላይ የሞት ቅጣት ተፈጸመባቸው

–ከጊዜያዊ መቃጸሪያ አስተዳደር ደርግ የተሰጠ መግለጫና ውሳኔ

በአብዮትና በደረ አብዮት ኃይሎች መካከል ያደረን ግንኙነት ቃሳቁ አብዮታዊ መሪ ሊቀ መንበር ማሉ በሚ ነባ ገልጹውታል ።

ደረ አብዮተኞች ቀዳሪና አዋዴ ኃይል ናቸው ። አለ'ግኒ ነገ፪ ኃይሎ ችን የሚያወጡ ኃይሎች ናቸው ። ያለፕርፕር የለየላቸው ደረ አብዮተ ኞች ሲሉመው አይችሉም ። ሆኖም በህዛችን ተጨባጭ ሁኔታ መሠ ረት አብዮኞቹ በረ አብዮተኞች በብ ዙም ሆነ በተቂቱ የሲላ ኃላ ይሰወ ሳሉ ። የምንከተለው መመረያ ቅክ ክል በመሆኑ ብዙዎቹ የአብዮቱ ተባ ራዴ ከመሆን የተቀላቀቁ ቢሆኑ ፣ እን ሳንዶቹ እንዲያውም መልካም ተግባ ርን እኔናውንተል ። በመጀመሪያ በዞ ይና በ[illegible] ጉ- ም- እና በ[illegible] ጉ- ም- የተደረገው ደረ አብዮተኞችን የመደምሰስ ተግባር እስደለጊ እንጂ ነበር መታወቅ አለበት ። እያንዳን ዱን ደረ አብዮተኛ እንደ ተራ ሁኔታ መቅጣት እስደለጊ ነው ። ከዚይ በተ ጠሱት ዓመታት ባደረግነው የደረ አብዮተኞች መደምሰስ ዘመቻ እያል ሰዎችንስሞት ተቀብተናል ። ይህ ትግል የተፈጸመባቸው ምን ዓይነት ሰዎች ነበሩ ? እነዚህ ደረ አብዮተኞች የሰ ፈው ሕዝብ በመሠር የተጠፀሙ ነበሩ። ስድስት መቶ ሚሊየን ሕዝብን በሚ ያጠቃልል ታሳት አብዮት ውስጥ የታ ወቁትን አምባ ነነንና ፈላጭ ቆራጭ ገዢዎችን በሞት በንቀጠ ናር ሲደው ሕዝብ በደህ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ አይነግም ነበር ። ደረ አብዮተኞችን መደምሰስ እውነ ትኛ ትግል ነው ። መንገዱ ለዘ ከዳድ ሥራን ይጠይቃል ። መሠናክት የለዳሉንም ። ሆኖም ከዚህ ሁሉ ችግር ጀርባ ሰላማዊ ሕዝብ ተመርጦ የተበጎ ሊት መገበር ከሆነ በኋላ የለለውን ነገር ለመፍጠር አስቸጋሪ አይደለም ።





በዚህ መሠረት ኅረመኔውና ደረ አብዮተኛው ግርማ ከበደም የአብዮቱ ወዳጅ የሞቀት ሕዝብ አጋር በመሆ ሰል በለደው ሕዝብ ተመርጦ የተበጎ ሊት መገበር ከሆነ በኋላ የለለውን ነገር ለመፍጠር አስቸጋሪ አይደለም ።

በአረመኔው ግርማ ከበደና በግብረ አበሮቹ ላይ ...

## የኢሕአፓው አመራር አባል ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ

# ተስፋዬ ተስፋ ሁነን

(39ኛውን የሙት ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ)

በዕለተ ሐሙስ ፣ ወርሃ መጋቢት
በወሩ አጋማሽ ፣ ልክ በአሥራ አምስት
ሺህ ዘጠኝ መቶ 69 ዕለት
ሺህ ሰው አሸለበ ፣ ባንድ ጀግና እልፈት።
የትግል ዓርማ ዝቅ አለ ፣ ሰማዩ ደመነ
ዕምባዎች ጐረፉ ፣ ትግል ሀዘን ሆነ።
አየሩ በረደ ፣ ዝቅ አሉ መፈክሮች
ህዋሳት ፈዘዙ ፣ ተወጉ ስሜቶች።
ኢሕአፓን መታው ሀዘን ፣ ብርሃን ጨለመ
የትግል ሕይወቱ ፣ እጅጉን ታመመ
ተቀማ መሪውን ፣ ሩቅ አሳቢውን
ባጭሩ ቀጠፉት ፣ ዕምቡጥ አበባውን።
ከራሱ ተመታ ፣ ቅስሙ ተሰበረ
ተስፋ ልጁን አጥቶ ፣ በቁጭት አረረ።
ጉልበቱ ሸብረክ አለ ፣ ወገቡ ተቀጨ
ገና ሳይፈተል ፣ ነጠላው ተቋጨ።

ወጣቶች እየዬ አሉ ፣ እናቶች ደረት መቱ
አባቶች ተከዙ ፣ እህቶች ዋተቱ
ተስፋዎች ጠወለጉ ፣ መንገዶች ራቁ
ጽሁፎች ደበዘዙ ፣ ቀለሞች ደረቁ
ክንዶችም ዛሉ ፣ አንደበቶች ተዋጡ
ጣቶችም ታጠፉ ፣ ዓይኖች ብርሃን አጡ
ጆሮ ጉዱን ሰማ
ከሕንፃው ከማማ
“ጀግና እራሱን ወ...ረ...ወ...ረ...፣
ሞተ አሉ ተ...ቀ...በ...ረ...።”
አንድ ልጇን አጣች ፣ ምድር በደም ታጥባ
ተስፋዬ ሞቶባት ፣ ስትጮህ ስታነባ።

መሠረተ ደሃ ለጭቁን የቆመ፣
ሀገር ያስቀደመ
ሕይወቱን ለትግል ፣ ዕውቀቱን ለትግል
አሳልፎ የሰጠ ፣ የዓላማ አክሊል
እኔስ ለኢትዮጵያ ፣ ለእምዬ ሀገሬ
ትምህርቴም ለእሷ ነው ፣ ለድሃው ገበሬ
ምሁር ለሕዝብ! ፣ ምሁር ለሀገር!
አርሶ ላስተማረኝ ፣ ያገሬ ባለሀገር
በላቡ ላስከበረኝ ፣ ለኢትዮጵያ ላብ አደር
አለብኝ ምከፍለው የትላንት፣
የአምናና ካቻምና ያላለቀ ብድር
ብሎ የተነሳ ፣ ተስፋዬ ተወለደ ከኢሮቦች መንደር።

እሱነቱን ለሕዝብ ፣ በደም የለወጠ
ለሰው ልጆች መብት ፣ ዕውቀቱን የሰጠ
የሕዝብን አደራ ፣ ለንዋይ ያልሸጠ
ለኢትዮጵያ ሀገራችን ፣ ዘብ ሆኖ የቆመ
ያ የጀግና ልጅ ፣ ከአሲምባ ያለመ
ከታጋዮች መሃል ፣ ገብቶ ያታገለ
ገብቶ የታገለ
በትግል መሞትን ፣ በተግባር ያሳየ
የትግል መምህር ፣ ይታወስ ተስፋዬ።

“ቢወቀጥ አጥንቴ ፣ ቢንቆረቆር ደሜ”
ታይቷል በተስፋዬ ፣ ለሀገር ልምላሜ
“ፍፁም ነው እምነቴ ፣ የትግሉ ነው ሕይወቴ”
እስከዘለዓለሙ ፣ ተጽኗል በደምህ
ሁሌም ይዘመራል ፣ በጀግና አንደበትህ።

ለአምባገነን መንግሥት ፣ ሕዝብን ላልወከለ
ሥጋህ አልተገዛም ፣ ሳለ እየታገለ
ጭራ ለቆሉቱ ፣ ለባንዳ ምሁራን
አርአያ ቴዎድሮስ ፣ አልሰጠህ እጅህን
በአጥንት በደምህ ፣ ጽፈሃል ታሪክን ።

ተስፋዬ ፦ የሀገር አበባ
የትግል ካባ
የጭቁን መምህር
የሕዝብ አምባሳደር
ሕይወትህ ላብ አደር
ኑሮህ ለአርሶ አደር
የምሁር አርአያ
ጽናትህ መለያ
ፍቅርህ ኢትዮጵያ።

አንት የትውልድ አውራ ፣ ስምህ ዳግም ያብራ
ተስፋህም ይለኮስ ፣ ይሁንን ደመራ
ገና ይቀርሃል ፣ መች ደረስህ ከግብ
ይታፈስ ደምህ ፣ ይሰብሰብ አጥንትህ
ለኢትዮጵያ ሀገራችን ፣ ዘብ ይቁም መንፈስህ።
አጥንትህ ይሸከም ፣ መለያ ዓላማውን
ደምህም ያለምልም ፣ የሕዝብ አንድነትን
ተስፋዬ ተስፋ ሁነን
እኛስ አንቀላፋን . . .
እኛስ አንቀላፋን. . .
መንፈስህ ይ..ቀ..ስ..ቅ..ሰ..ን..።

ስለ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ የሕይወት ታሪክ ለማንበብ ቀደም ሲል በ«ያ ትውልድ ተቋም» የተዘጋጁትን ጽሁፎች ቀጥሎ ባለው ማገናኛ በመጠቆም ያንብቡ።

- መጋቢት 15 ቀን 2005

http://yatewlid.com/index_htm_files/032413%20Dr.%20Tesfay%20Debesay.pdf

- መጋቢት 15 ቀን 2007

http://yatewlid.com/index_htm_files/Ya_Tewlid_Vol_2_LeyuItem_Megabit_15_2007.pdf

በመጨረሻም «ያ ትውልድ ተቋም» በተለይ የያ ትውልድ ታሪክ ሲነሳ በእንቅስቃሴው የተከሰቱ በርካታ ስህተቶች ቢኖርም በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ የመንግሥትን ሥልጣን ይዞ ትውልድ ያጠፋ እንደ ደርግ አገዛዝ አልነበረምና ዳግም እንዳይከሰት ማስተማሪያ ሊሆን የሚችለው ታሪኩ ሲጻፍ ነው እንላለን። የገዳዮችና የጨፍጫፊ ገሾዎች ታሪክ ዳግም እንዳይደገም ካስፈለገ የተደረገውን መጻፍ፣ ማሳወቅ አስፈላጊነቱን ደጋግመን ማሳሰብ እንወዳለን።

ጊዜው ምን ቢረዝም ወንጀል ወንጀል ነውና ገዳይ ወንጀለኞች ለፍርድ መቅረብ ይኖርባቸዋል ስንል በመቶ ሺህ ለሚቆጠሩት እንደአብነት ለእነ ማርቆስ ሀጎስ፣ ለዳሮ ነጋሽ፣ ቤተሰቦች መሞገታችን ነው። ድምጽ አልባ ለሆኑት ሰማዕታት ድምጽ መሆናችን ነው። የገዳዮችን ወንጀላቸውንና ታሪካቸውን ደብቀን አስተማሪ ልናደርገው ከቶም ይከብዳል።

የወያኔ አገዛዝ በ1997 ዓ.ም. ምርጫን አስታኮ የአደረገው 193 ወገኖች ጭፍጨፋ በየአካባቢው በበደኖ፣ አርባ ጉጉና በተለያየ ወቅት ያደረገው ዘግናኝ ጭፍጨፋዎች፣ በእስላም ወገኖች ላይ የሚካሄደው ጭፍጨፋ፣ አሁንም በቅርቡ እየተካሄደ ያለው በተለይ በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የማያቋርጥ ጭፍጨፋ፤ የደርግ አገዛዝ ቁንጮዎች በአደረጉት ትውልድ ማጥፋት ተጠይቀው ቢሆን ኑሮ ዛሬ ባልተደገመ። ፋሽስት መንግሥቱ ኃይለማርያም በመቶ ሺህ የሚቆጠር ቤተሰብ ቤት ዘግቶ ያለምንም ተጠያቂነት ሲቀመጥ ቀጣይ መሪዎችስ "ማን ይነካናል? ጨፍጭፈንና ዘርፈን የምንሄድበት አናጣ" ቢሉ ምን ይፈረድባቸዋል? በተለያዩ ዓለማት አድፍጠው ያሉ መሰል ግርማ ከበደዎችን ለፍርድ ለማቅረብ ካልተጣረ ነገ የወያኔ ተጠያቂዎችንስ "እንዴት ተደርጎ?" ቢያሰኝ ምን ያስደንቃል።

"ያደረግነው ጭፍጨፋ የለም ቢኖርም ትክክል ነን" ከማለት አልፈው ያንንኑ የጨረሱትን ትውልድ አጽም ተጠያቂ እያደረጉ ዳግም እየገደሉ ሲጽፉብን "በርቱ ባዮች" ከሆንን ነገም የወያኔ መንግሥት ሲፈረካከስ በአደረሱት ጥፋት ለፍርድ ከማቅረብ ይልቅ ስብሐት ነጋ፣ በረከት ስምዖን፣ ስዩም መስፍን... እየተፈራረቁ ትግላችን፣ ትዝታችን፣ ትውስታችን ቢሉን በማን ይፈረዳል?

ወያኔ የደርግን ቀጣይ ሥራ እንደሚያከናውን ሲመጣም ያውቀዋልና እንዴት ተደርጎ ሀገር ገዳይ ሕዝብ ገዳይ ላይ ይጨክናል? በባህሪ አንድ የሆኑ ገዥዎች የቀዳሚውን ገዳይና ዝርፊያ ታሪክ በመደበቅ ወይም ልክ እንደነበርና ትክክለኛውን ታሪክ ጥላሸት በመቀባትና በማወላገድ ለነሱም ይኸው ይቀጥልላቸው ዘንድ ሲያመቻቹ መታዘብ እራሳችንንም በታሪክ ከተጠያቂነት አዙሪት ውስጥ እንደሚከተን መረዳት ይኖርብናል።

በሀገርና ሕዝብ ላይ የሠሩት ወንጀል እንዳይነሳባቸው "ጊዜው የትግል ነውና እሱን አታንሱት" ሲባል "ትግል እኮ ወንጀለኛን ለሥልጣን ለማብቃት አይደለም" ካላልን ትግል ምኑን ትግል ሆነ? ትላንት ከደርግ ጋር በቤት ለቤት አሰሳው፣ ነፃ እርምጃው፣ ቀይ ሽብሩ አብረው ሲጨፍሩ የነበሩ ዛሬ "ተዋቸው" ተብሎ የትግል መድረክ ተሰጥቷቸው ለዳግም ሥልጣን ሲያኮበኩቡ ከዝምታም አልፈን ልናቅፍ የምንደረደር ከሆንን ትግል ምኑን ትግል ሆነ?

«ያ ትውልድ ተቋም" በደርግ አንድ ትውልድ ማጥፋት ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ሰለባ ለሆናችሁ ወገኖች ምንጊዜም ልሳናችን አይዘጋም፣ ብዕራችን አይነጥፍም። ሌላ ቢቀር ለቤተሰቦቻቸውና ለመከራው ገፈት ቀማሾች ታሪካቸውን በመዘከር ለሌሎች እናስነብባለን። እውነተኛውን ታሪካቸውን ለትውልድ ለማስተላለፍ መረጃ የማሰባሰባችን ቀጣይነቱን ስናሰምርበት የበርካታ ወገኖች ድጋፍና ትብብራችሁን እያመሰገንን ነው። ገድላችሁና ታሪካችሁ ሁሌም ከመቃብር በላይ ስለሆነ ነው ሲጀመርም "በትግል መሞት ሕይወት" ያልነው።

«ያ ትውልድ ተቋም» ለመረጃ ምንጭነት!
የተገፉ ወገኖችን ለመርዳት!
ለያ ትውልድ መታሰቢያነት!

**ዋቢ ማጣቀሻና መረጃዎች፡**


- የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ፡ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡ 2ኛ ዕትም 1961 ዓ.ም.፡ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
- አዲስ ዘመን ዕለታዊ ጋዜጣ መጋቢት 1969 ዓ.ም. ዕትሞች
- አደራ ልዩ ዕትም፤ ግንቦት 2001 ዓ.ም. የሰማዕታት ሐውልት ግንባታ ማህበር፡ አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ
- ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ እውነተኛ ታሪክ፡ ቅጽ አራት፡ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት 1991 አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ
- ያ ትውልድ ቅጽ 3፡ የለውጥ ማዕበል በኢትዮጵያ የኢሕአፓ ታሪክ፡ ክፍሉ ታደሰ 2ኛ ዕትም ሐምሌ 1993 ዓ.ም.
- ፍፁም ነው ዕምነቴ ቀይ ሽብር የከፋተኛ 15 ዕውነተኛ ታሪክ፡ ነሲቡ ስብሐት 2ኛ ዕትም መስከረም 2008 ዓ.ም. ሰሜን አሜሪካ



**«ያ ትውልድ ተቋም»**

- ኢሜል : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com
- ድረ ገጽ : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org
- ምስለ ገጽ : yatewlid